የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጉምሩክ ኮሚሽን

FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
CUSTOMS COMMISSION

ቁጥር/ Ref.No. 4/0703/13
ቀን/Date ህዳር 0 4 2013

በአባሪው ለተዘረዘሩት የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች በሙሉ
በያሉበት

የኢፌዴሪ ገንዘብ ሚኒስቴር በቁጥር ታ/ክ/ቀ/5/86 ህዳር 02 ቀን 2013 በተጻፈ ደብዳቤ ከቀረጥና ታክስ ነጻ ሆነው ወደ ሀገር ከገቡ በኋላ ሀገር ውስጥ በሚሸጡ እንዲሁም በጊዜያዊነት ከቀረጥና ታክስ ነጻ ሆነው ወደ ሀገር ከገቡ በኋላ ተመልሰው በሚወጡ ወይም በሀገር ውስጥ በሚሸጡ ተሽከርካሪዎችና ማሽነሪዎች ላይ የኤክሳይዝ ታክስ የሚሰበሰብበትን ሁኔታ መወሰን አስፈላጊ ሆኖ መገኘቱን በመግለጽ፡-

1. ከቀረጥና ታክስ ነጻ ሆነው ወደ ሀገር የገቡ ተሽከርካሪዎች እና ማሽነሪዎች ሀገር ውስጥ በሚሸጡበት ጊዜ ወደ ሀገር በገቡበት ጊዜ የነበራቸውን የአገልግሎት ዘመን (ዕድሜ) መሠረት በማድረግ በዚሁ የአገልግሎት ዘመን ላይ የሚገኙ ተሽከርካሪዎችና ማሽነሪዎች ወደ ሀገር ሲገቡ በሚከፈለው መጣኔ መሠረት የኤክሳይዝ ታክስ እንዲከፈልባቸው፤

2. በጊዜያዊነት ከቀረጥና ታክስ ነጻ ሆነው ወደ ሀገር የገቡ ተሽከርካሪዎች እና ማሽነሪዎች ተመልሰው ከሀገር በሚወጡበት ወይም በሀገር ውስጥ ተመሳሳይ መብት ለሌለው ሰው በሚተላለፉበት ጊዜ ወደ ሀገር በገቡበት ጊዜ የነበራቸውን የአገልግሎት ዘመን (ዕድሜ) መሠረት በማድረግ በዚሁ የአገልግሎት ዘመን ላይ የሚገኙ ተሽከርካሪዎችና ማሽነሪዎች ወደ ሀገር ሲገቡ በሚከፈለው መጣኔ መሠረት በእርጅናው ቅናሽ ዋጋ ላይ ቀረጥና ታክስ እንዲከፈልባቸው የተወሰነ መሆኑን በመግለጽ ከቀረጥና ታክስ ነጻ ሆነው እንዲሁም በጊዜያዊነት ከቀረጥና ታክስ ነጻ ሆነው ወደ ሀገር በገቡ ተሽከርካሪዎች ላይ የኤክሳይዝ ታክስ አከፋፈል ከዚህ በላይ በተመለከተው መሠረት እንዲፈጸም አሳውቋል፡፡

በመሆኑም ከቀረጥና ታክስ ነጻ ሆነው እንዲሁም በጊዜያዊነት ከቀረጥና ታክስ ነጻ ሆነው ወደ ሀገር በገቡ ተሽከርካሪዎች ላይ የኤክሳይዝ ታክስ አከፋፈል በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ውሳኔ መሠረት ተፈጻሚ እንዲደረግ እያሳሰብኩ፤ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ውሳኔ የሰጠበትን 02 ገጽ ደብዳቤ አባሪ በማድረግ የተላከ መሆኑን አሳውቃለሁ፡፡

ከሠላምታ ጋር

ደበሌ ቃበታ ሁርሳ
የጉምሩክ ኮሚሽን ኮሚሽነር

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የጉምሩክ ኮሚሽን ቁጥር 1
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Customs Commission No.1

ግልባጭ፤
- ለኮሚሽን ጽ/ቤት
- ለጉምሩክ ኦፕሬሽን ዘርፍ
- ለህግ ተገዥነት ዘርፍ

ጉምሩክ ኮሚሽን

ደረጃውን የጠበቀ ዘመናዊ የጉምሩክ አስተዳደር እንዲሰፍን ተግተን እንሰራለን !

ስልክ/Tel:- +251 116 62 98 00
:- +251 116 62 98 19
ፖ.ሳ.ቁ. 2559

Email: customscommission@gmail.com
Website:- www.ecc.gov.et

አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia

- ለአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሞጆ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዳማ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለድሬዳዋ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
- ለጅግጅጋ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለመቀሌ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለኮምቦልቻ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለባህርዳር ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአሶሳ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጅማ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሀዋሳ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሞያሌ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዋሽ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሠመራ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጋላፊ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጅቡቲ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት
- ለታጁራ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት

<u>በያሉበት</u>፡

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ገንዘብ ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Finance


ቁጥር / Ref.No ተ/ፍ/ቁ/5/86
ቀን / Date 02 ህዳር 2013

ለጉምሩክ ኮሚሽን
<u>አዲስ አበባ</u>

ከኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 1186/2012 የፖሊሲ ዓላማዎች አንዱ በአየር ንብረት ላይ ከፍተኛ ጉዳት በማስከተል ላይ የሚገኙት ያገለገሉ ተሽከርካሪዎች እና ማሽነሪዎች ወደአገር እንዳይገቡ መከላከል እንደሆነ ይታወቃል፡፡

አዋጁ ተሽከርካሪዎች እና ማሽነሪዎች ወደአገር ከገቡ በኋላ አገር ውስጥ የሚሰጡትን አገልግሎት ከግምት ውስጥ በማስገባት የኤክሳይዝ ታክስ እንዲከፈልባቸው የማይደነግግ በመሆኑ የታክሱን ፍትሐዊነት ለማረጋገጥ እንዲሁም የሕግ አፈፃፀሙ ከፖሊሲው ጋር የተጣጣመ እንዲሆን ለማድረግ ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው ወደአገር ከገቡ በኋላ አገር ውስጥ በሚሸጡ እንዲሁም በጊዜያዊነት ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው ወደአገር ከገቡ በኋላ ተመልሰው በሚወጡ ወይም በአገር ውስጥ በሚሸጡ ተሽከርካሪዎችና ማሽነሪዎች ላይ የኤክሳይዝ ታክስ የሚሰበሰብበትን ሁኔታ መወሰን አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በመሆኑም በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 1186/2012 አንቀጽ 42(2) እና በጉምሩክ አዋጅ አንቀጽ 71(9) ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ለአዋጁ ትክክለኛ አፈፃፀም ሲባል፣

1. ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው ወደአገር የገቡ ተሽከርካሪዎች እና ማሽነሪዎች አገር ውስጥ በሚሸጡበት ጊዜ ወደአገር በገቡበት ጊዜ የነበራቸውን የአገልግሎት ዘመን (ዕድሜ) መሠረት በማድረግ በዚሁ የአገልግሎት ዘመን ላይ የሚገኙ ተሽከርካሪዎችና ማሽነሪዎች ወደአገር ሲገቡ በሚከፈለው መጣኔ መሠረት የኤክሳይዝ ታክስ እንዲከፈልባቸው፣

2. በጊዜያዊነት ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው ወደአገር የገቡ ተሽከርካሪዎች እና ማሽነሪዎች ተመልሰው ከአገር በሚወጡበት ወይም በአገር ውስጥ ተመሳሳይ መብት ለሌለው ሰው በሚተላለፉበት ጊዜ ወደአገር በገቡበት ጊዜ የነበራቸውን የአገልግሎት ዘመን (ዕድሜ) መሠረት በማድረግ በዚሁ የአገልግሎት ዘመን ላይ የሚገኙ ተሽከርካሪዎችና ማሽነሪዎች ወደአገር ሲገቡ በሚከፈለው መጣኔ መሠረት በእርጅናው ቅናሽ ዋጋ ላይ ቀረጥና ታክስ እንዲከፈልባቸው፣

ተወስኗል፡፡

በኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን
Ethiopian Customs Commission Records Documentation No.1

Lette.B/GT

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
ገንዘብ ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Finance

ቁጥር
Ref.No ታ1ጀገ/ፋ15/86
ቀን
Date 02 ህዳር 2013

ስለዚህ ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው እንዲሁም በጊዜያዊነት ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው ወደአገር በገቡ ተሽከርካሪዎችና ማሽነሪዎች ላይ የኤክሳይዝ ታክስ አከፋፈል ከዚህ በላይ በተመለከተው መሠረት እንዲፈፀም እናሳስባለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ * ገንዘብ ሚኒስቴር 2

ኢዮብ ተካልኝ (ዶ/ር)
ሚኒስትር ዴኤታ

ግልባጭ፣
ለገቢዎች ሚኒስቴር
<u>አዲስ አበባ</u>

ለክቡር ሚኒስትር ጽ/ቤት
ለክቡር የፊሲካል ፖሊሲና ፐብሊክ ፋይናንስ ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ
ለክብርት የኢኮኖሚ ትብብር ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ
ለሕግ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት
ለታክስ ፖሊሲ ዳይሬክቶሬት
<u>ገንዘብ ሚኒስቴር</u>

በኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን
ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.1
Ethiopian Customs Commission
Records Documentation No.1

Lette.B/GT

ስልክ
Tel 251- 11- 155 24 00,22 66 98
251- 11- 155 00 81,83 86 89
የፖ.ሣ.ቁ
P.O.Box 1905,1037
እባክዎን መልስ ሲፅፉልን የኛን ቁጥር ይጥቀሱ
ፋክስ
Fax 251-11-156 01 24,55 14 96
251-11-155 11 38
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa-Ethiopia